



## ⚠ ልብ ይበሉ

# የእብድ ውሻ በሽታ

### ገዳይ ቢሆንም ውሻዎን በየጊዜው ተከታትለው በማስከተብ በሽታውን ሙሉ በሙሉ ሊከላከሉት ይችላሉ!!!

### ቅድመ - ጥንቃቄ




- ውሻዎን ያስከትቡ፣ ይንከባከቡ፣ ይቆጣጠሩ፣በአቅራቢያዎ በሚገኝ የእንስሳት ክሊኒክ ያስመዝግቡ።
- የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎችን በመጠበቅና በመንከባከብ በቤትና በዱር እንስሳት መካከል የሚከሰትን የእብድ ውሻ በሽታ ዝውውርና ስርጭት ይከላከሉ።

### አንድ ሰው በውሻ ከተነከሰ በኋላ ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎች



- የተነከሰውን የሰውነት አካል (ቁስል) ወዲያውኑ በንፁህ ውኃ እና በሳሙና ያለማቋረጥ ለ15 ደቂቃ ይጠቡ።
- ከተቻለ ቁስሉን በቁስል ማፅጃ ይጥረጉ።
- በተቻለ ፍጥነት በአቅራቢያ ለሚገኝ ጤና ተቋም ሪፖርት በማድረግ የህክምና ዕርዳታና ምክር ያግኙ።

### በንክሻ ጉዳት ባደረሰ ውሻ ላይ ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎች



- ውሻው በበሽታ የተጠረጠረ ከሆነ በፍጥነት በቁጥጥር ሥር አውለው ለእንስሳት ጤና ክሊኒክ ይጠቁሙ።
- ውሻው በበሽታው ያልተጠረጠረ ከሆነ ከ10-14 ቀናት በተገለለ ሥፍራ አሥሮ ምግብና ንፁህ ውኃ እያቀረቡ በማቆየት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የእብድ ውሻ በሽታምልክቶች ከታዩበት በፍጥነት ለእንስሳት ጤና ክሊኒክ ይጠቁሙ።

## እራስዎን፣ ቤተሰብዎን እና እንስሳትን ከእብድ ውሻ በሽታ ይጠብቁ!

Global Affairs Canada

alinea

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE